# አገር እንደ ዳቦ

አገር እንደ ዳቦ እየተቆረሰ፣

ከሰላ ተበልቶ ጅቡቲ ደረሰ፣

ጅቡቲ ተበልቶ ኤርትራ ደረሰ፣

ኤርትራ ተበልቶ ሁመራ ደረሰ፣

ለጎራሽ (ለጠላት) እንዲያመች እየተገመሰ።

እየተሸረፈ እየተቆረሰ፣

ዳር ዳሩ ተበልቶ መሃል ተደረሰ።

ይኸ ተላላኪ እንግዳ አስተናጋጅ እየተጣደፈ፣

ኦጋዴን ለማብላት፣

ወለጋን ለማብላት፣

ጋምቤላን ለማብላት

አፋርን ለማብላት፣

ትግራይን ለማብላት፣

እየሸነሸነ አገር ለማስበላት፣

በክልል፣በጎሳ ቆራሽ አሰለፈ።

የውጭ ወራሪ ሌላ መንገድ ቢያጣ፣

አገሩን ለመያዝ (ለመግዛት) መለስ ብሎ መጣ።

ከሰሃራ በታች ከሱዳን ባሻገር፣

ከኬንያ ወዲህ በኢትዮጵያ ድንበር፣

መሬትና ቦታ መግዛት ካማራችሁ፣

ብዙም አትከፍሉት፣ እርካሽ ነጋዴ መለስ አለላችሁ።

ጣልያንና እንግሊዝ ከአምሳ ዓመት በኋላ ከኢትዮጵያ በወጡ፣

ኢህአዴግን ፈጥረው እንደገና መጡ፣

በዲሞክራሲ ስም ከፋፍለው ሊግጡ።

የተፈጥሮ ንብረት መአድን ሊያወጡ፣

በርካሽ ሸምተው በውድ ሊሸጡ፣

ያገር ውስጥ ነጋዴ መድረሻ ሊያሳጡ።

በስመ ፈላሻ፣በስመ ሎተሪ ሕዝብን እያሶጡ፣

ፊደል የቆጠረ ትውልድ እያሳጡ፣

መለስ ቀለስ ብለው ለመበተን መጡ።

ወያኔን አስታጥቀው ሥልጣን ላይ አወጡ።

ጥንትም ሰሜኑ ነው መግቢያና መውጫቸው፣

ወደ መሃል አገር መረማመጃቸው።

ኢራን፣ ሕንድ፣ ቻይና፣ ቱርክና እሩስያ፣

አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ሳውዲ አረብያ፣

እስራኤል፣ኢሚራት፣ ደቡብ ኮሪያ፣

ካፍሪካም እንዲሁ ሳትቀር ኬንያ፣

በቅርጫው ገብተዋል በነጻው ገበያ፣

ወግድ ባይ  በሌላት በኢትዮጵያ።

ያገሬ ደሃ ሕዝብ አትቀበላቸው፣

ከንግዱ ባሻገር ሌላ ግብ አላቸው።

ለውስጡ ተነፍጋ ለውጭ የቀረበች፣

እየተገመሰች፣እዬተቆረሰች፣

ኢትዮጵያ አገራችን ክብ ዳቦ ሆነች፣

በዚህ ከቀጠለ ሙልሙል ትሆናለች።

ያለም ነጋዴዎች ካለፈው ተማሩ፣

ሕዝብ ስልጣን ሲይዝ በባዶ እንዳትቀሩ፣

ከወያኔ ጋራ አትፈራረሙ አትደራደሩ፣

የሱ ብቻ አይደለም የሰማንያ ሚሊዮን ሕዝብ ነው አገሩ።

አገር አፍ አውጥታ ጮሃ ትጣራለች፣

አድኑኝ አድኑኝ አድኑኝ ትላለች።

እናድናት!!!

አገሬ አዲስ

ነሃሴ 2002 ዓ.ም. (ሴፕቴምበር 2010)